# ስለሚመጣው መልካም እረኛ እነማን ሰበኩ?

የተሰጠውን ተስፋ ለመፈጸም የመሲሁን መልካም እረኝነት ለመግለጽ የጠፋውን በግ ሊፈልግና ሊያድን እንደሚመጣ የሚሰብኩ መምህራን በዚያን ዘመን ይፈልጉ ነበር ። በዚሁ መሠረት በብሉይ ኪዳን ጊዜ በየዘመኑ ከላይ ስለተነገሩት ነገሮች ትንቢት ይናገሩ የነበሩት ነቢያት ናቸው ዘመኑም ስብከት ተብሎ ተሰይሞአል የሰበኩለትም ስለትንቢት ሁሉ እና ስለ አባቶች ተስፋ ፈጻሚ ስለሆነው ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም ስለ ስብከታቸውና ስለምስክርነታቸው አገልግሎት ሲናገር እንደሚከተለው አቅርቦታል ። "ለእናንተም ስለሚሰጠው ጸጋ ትንቢት የተናገሩት ነቢያት ስለዚህ መዳን ተግተው እየፈለጉ መረመሩት በእነርሱም የነበረ የክርስቶስ መንፈስ እለ ስለ ክርስቶስ መከራ ከእርሱም በኋላ ስለሚመጣው ክብር አስቀድሞ እየመረመረ በምን ወይም እንዴት ባለ ዘመን እንዳመለከተ ይመረምሩ ነበር" ብሏል ። ፩ኛ ጴጥሮስ ም-፩-ቁ-፲—፲፩ ።

ሐዋርያው እንዳለው ነቢያት ለሕዝብ መድኃኒትና ጠባቂ የሚሆነውን መልካም እረኛ ፈልጉ መረመሩ ይሁን እንጂ በዘመኑ የነበሩት እረኞች ለበጐቻቸው የማያዝኑና የማይራሩ ራስ ወዳድ ስለነበሩ የክፋዎችን እንደክፋታቸው የመልካሞቹን እንደመልካምነታቸውና እንደደግነታቸው በጠቅላላው እንደሥራቸው ትንቢት ተናግረውላቸዋል ።

ከነዚሁ ነቢያት መካከል ነቢዩ ሕዝቅኤል ስለ ክፉ እረኞች የሚከተለውን ትንቢት ተናግሮላቸዋል። "እራሳቸውን ለሚያሰማሩ ለእስራኤል እረኞች ወዮላቸው እረኞች በጐችን ያሰማሩ ዘንድ አይገባቸውምን? ሥጋውን ትበላላችሁ ፤ ጠጉሩንም ትለብሳላችሁ የወፈሩትንም ታርዳላችሁ ፤ በጐቹን ግን አታሰማሩም ፤ የደከመ

እረኛ ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ በትምህርት ልንጠራቸው ይገባል በኃጢአት ተሰናክለው የወደቁትንም በትምህርት ፡ በንስሐ መልስን ወደ መልካሙ እረኛ እንዲመጡና ቤተሰብ እንዲሆኑ ፈልጎ ማቅረብ አለማችን ነው ባዝነው የጠፉትንም በትምህርት ፈልገን አስተምረን በፍቅር ፡ በሰላም ወደ ክርስቶስ እንዲመለሱ ማድረግ የዘወትር ተግባራችን ሊሆን ያሻል።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ